## *እውነተኛ መንፈሳዊነት ፣ ወንድማዊ መተሳሰብና ፍቅር*

***እውነተኛ መንፈሳዊነት*** - እግዚአብሔርን ከመውደድ (ለጌታ ካለን ፍቅር) የተነሳ ለእርሱ የምንቀርበውን እውነተኛና ከልብ የሆነን አምልኮን ያመለክታል።

- እራሳችንን ከመውደድ ሳይሆን፣ ታወቅነትን ለመግኘት ሳይሆን፣ በሰዎች ፊት ለመታየት ሳይሆን፣ - በእግዚአብሔር የምንታይና የምንመዘን መሆናችንን አውቀን፣ የጌታ ፍቃድ የምንፈፅም ከሆነ ይህ እውነተኛ መንፈሳዊነት ነው።(2ጢሞ3፡1-5)
- ጌታ ኢየሱስ - እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበት እውነተኛ ስጦታ (ምፅዋት)፣ እውነተኛ ፀሎት፣ እውነተኛ ጾም ምን እንደሆኑ በተራራው ስበከት ላይ ለደቀመዛሞርቱ አስተምሮአል። ማቴ6፡1-18.
- ስለዘህ እውነተኛ መንፈሳዊነት - ሰዎች በትምህርታችን፣ በአምልኮአችን፣ በአገልግሎታችን፣ ተመርከው እንዲደነቁ ሳይሆን -
    - ለጌታ የለንን ፍቅር በህይወታችን አይተው - በጌታ ፍቅር የሚመረኩ
    - በአገልግሎታችን - ለእግዚአብሔር ምርኮ የሚሆኑ
    - በአምልኮአችንን ውስጥ - ከእስራታቸው የሚፈቱ፣ የሚፈወሱ መሆን አለበቸው።
    - የጌታ ደቀመዝሙር ለመሆን፣ አሁን ለለንና ወደ ፍት ለምጠብቀን ህይወት፣ እንደሁም ከጌታ ዘንድ የሚያስፈልገንን ሃይል ለመቀበል እውነተኛ መንፈሳዊነት በህይወታችንን መኖር አለበት። (1ተሰ4፡1-2፣ 1ጢሞ4፡7-8፣ 1ጢሞ6፡6፣ ማቴ6፡33፣ ማር10፡28-30)
    - በመጨረሻው ዘመን - ዓለም፣ ምድርና በውስጧ የሉ ስራዎች ሁሉ ይጠፋሉ። ስለዚህ ሃሳባችንን በጌታ ፅድቅ ሥራና በእውነተኛ መንፈሳዊ ህይወት ላይ ማድረግ አለብን። (2ጴጥ3፡10-13)

### *እውነተኛ መንፈሳዊነት በህይወታችን እንዴት ያድጋል።*

1. እውነተኛ መንፈሳዊነት በህይወታችን ለማደግ - እራስን ማሰልጠን ያስፈልጋል። (1ጢሞ4፡12-16)
2. እውነተኛ መንፈሳዊነት በህይወታችን እንዲያድግ - እራስን ማሰልጠን ብቻ ሳይሆን - እራሳችንን ከማይጠቅም፣ እንቅፊት ከምሆኑብን ነገሮች ማግለል አለብን። (ቲቶ2፡11-12)

## *ወንድማዊ መተሳሰብና ፍቅር*

***ወንድማዊ መተሳሰብ፤*** ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው ልኖራቸው የሚገበውን መወደድ፣ መደጋገፍ፣ መከባበርና መፈቀርን ያመለክታል። (ዕብ13፡1፣ 1ተሰ4፡9-10፣ 1ጴጥ1፡22፣ ሮሜ12፡10)

***ፍቅር፡*** ክርስቲያን ወንድምን (እህትን) ወይም ቤተሰብን ወይም ጓደኛን ብቻ ሳይሆን - የሚጠሉንን የሚጨምርን ነው። (ማቴ5፡44)

### *በወንድማዊ መተሳሰብና በእውነተኛ ፍቅር ህይወት እንዴት እናድጋለን።*

- እውነተኛ መወደድና ፍቅር በህይወታችን ልያድግ የሚችለው - መጀመሪያ የእግዚአብሔር ለእኛ የሰጠንን ፍቅር ምን ያህል እንደሆና ከተረዳን ብቻ ነው። (1ዮሐ4፡7-10፣ 1ዮሐ4፡11-12)
- በህይወታችን የፍቅርን ህይወት መለማመድ አለብን። (ኤፌ5፡2፣ ቆላ3፡14፣ 1ቆሮ16፡14፣ ገላ5፡13፣ ቆላ2፡2)
- እውነተኛ ፍቅር በህይወታችን የሚያድገው- በመጀመሪያ የእግዚአብሔርን ፍቅር በህይወታችን ስንገልፅ ብቻ ነው።(1ዮሐ5፡3)
- እግዚአብሔር ፍቅሩን በህይወታችን እንዲያሰድግ ዘወትር መፀለይ አለብን።(1ተሰ3፡12፣ ኤፌ3፡17-19፣ ፊል1፡9)